29 December 2016

**የአበበ በለው ሴራ በሄኖክ የሸጥላ ላይ**

በቅድሚያ አንባብያን ሶስት ነገሮችን እንዲረዱልኝ እጠይቃለሁ

፩ኛ፡ በስም የምጠቅሳቸውን ሰዎች ሁሉ ፕሮፌሰር ሆኑ ዶክተር፤ ኢንጅነር ወይንም ሌላ በስማቸው እንጅ የትምህርት ወይንም የሥራ ደረጃቸውን ተቀጥያ ጨምሬ እንዳልሆነ ይታወቅልኝ። የሚያገናኘን የኢትዮጵያ ፖለቲካ እንጅ ሙያችን ወይም ትምርታችን አይደለም። ይህ ኋላ ቀር የሆኑ ህብረተስቦች እና ግለሰቦች እራሳቸን ከፍ በማድረግ እኩልነትን ሳይሆን የበላይና የበታችነትን የሚያጠናክሩበት በተለይም ኢትዮጵያውያንን እጅግ የተጠናወተ የህሊና በሽታ በመሆኑ ልንታገለው ይገባናል። ይህ ግን ለሙያው ክብር የለኝም ማለት አይደለም። ሁሉም በቦታውና በወጉ ይሁን ነው የምለው።

፪፡ተኛ ሄኖክ የሺጥላ አንደበቱ ፍቱን ነው። ሃሳቡን ለሰሚው በትህትና በማያደናግር መልኩ ግልጽ አድርጎ የማቅረብ ችሎታና ስጦታ አለው። ይህን ችሎታውን ከማድነቅ አልፎ የሚናገረውን መረዳት ያቅታል የሚሉ እንደነ አበበ በለው ያሉ ካሉ የምጠራጠረው የነሱን ችሎታና ከጀርባ ያለውን ዓላም እንጅ ሄኖክን አይደለም። ይህ ችሎታው የሚያስቀናን እንጅ የሚያስወቅሰው አይደለም። የብርኃኑ ነጋ ንግግር ያዘለው መርዝ ሳይገባው መረቀኝ ብሎ የሚያጨበጭብ ሰው ችሎታው አጠያያቂ ነው።

፫፡ተኛ የሄኖክ ትችት እንደምላጭ የሰላ ነው። ትችቱን ሰው ምን ይለኛል በሚል ይሉኝታ ታጥሮ ወይንም ጠላት አበዛለሁ በሚል ፍርሃት ተሸማቆ መናገር ያለበትን ከመናገር አይቆጠብም። እውነትንና ማስረጃን እስከያዘ ድረስ የሚያግደው የለም። ይህ በኢትዮጵያ ፖለቲካ አልተለመደም። በዚህ መልኩ የሚያቀርባቸውን ትችቶች መቀበል የሚሳናቸው አበበና መሰሎቹ የሚተረጉሙት ስድብና ውሸት አድርገው ነው። መሟገቱ ስለሚያቅታቸው፤ ችሎታውም ስለሚያንሳቸው ሄኖክ ለክርክር አይመችም፤ የሚያውቀው ስድብ ብቻ ነው ብለው ያጥላሉታል። ሄኖክ ያደረጋቸው ቃለምልልሶችና ጽሁፎች ሁሉም ኢንተርነት ላይ ስላሉ አንባቢ የራሱን ድምዳሜ ያድርግ። ትክክለኛውን የሄኖክ ፌስቦክ ይመልከት። በመሆኑም አበበ ስድብ በሚላቸው ላይ ተጨማሪ ትችት የለኝም። ይህን ካልኩ በኋላ ወደተነሳሁበት ልመለስ።

አበበ በአዲስ ድምጽ ሬዲዮ ከሄኖክ የሺጥላ ጋር ያደረገው ቃለምልልስ ያልተሳካና ተንኮል ያዘለ ነበር። የቃለ ምልልሱ ዓላማ በሚገባ ተቀነባብሮ እንደወያኔ የውሸት ማስረጃ በማዘጋጀት የሄኖክን ማንነት በከሃዲነትና በውሸታምነት ስሎ አድማጭን በማሳመን ሄኖክን ማዋረድ ብሎም ከተሰለፈበት ቅዱስ አላማ መነጠል ነበር። ሆኖም ለሄኖክ የመዘዘውን ሰይፍ በራሱ አንገት ላይ አሳርፎታል። ብልጠት ሲበዝ ምንግዜም ቢሆን መጨረሻው አያምርም። ይህ ዓይነት ተንኮል በተደጋጋሚ ላለፉት ፳፫ ዓመታት በዓማራው ላይ ተፈጽሟል። ዓላማውም ዓማራውን ድርጅት አልባ በማደግ የመከላከል አቅሙን አኮስምኖ መጨረስ ነው። ወያኔ ታላቁን መሪ አሥራት ወልደየስን አሰቃይቶ ሲገድል፤ መስፍን ወልደማሪያም ዓማራ የለም ሲሉ፤ እነብርሃኑ ዓማራው ማነው እያሉ ሲያሟርቱ እንዳይደራጀ የተለያየ ተንኮል ሲሸርቡ ኖረዋል። ከብዙ ውጣ ውረድና መሰናክል በኋላ ዓማራው የተጋረጠበትን መሰናክል ፈነቃቅሎ በመውጣት የራሱን ድርጅት መፍጠሩ ለዓማራው ጠላቶችና የውሸት ነጻ አውጭዎች እንደ ኃይለኛ ሱናሚ ውስጣቸውን አናውጦታል። አሁን የምንሰማው ጫጫታ፤ የሃሰት ክስ፤ ስም የማጥፋት ዘመቻና ሌላ ሌላው ሁሉ ከውድቀት በፊት ራስን ለማዳን የሚደረግ መንፈራገጥ መሆኑን እንረዳለን።

የግንቦት ሰባት አባላት በጤናማ ፖለቲካ የተሰማሩ ሳይሆን አዙረው በማያዩ፤ አለቃቸውን ጥያቄ ውስጥ የማያስገቡ፤ ለምንና እንዴት ብሎ የማይጠይቁ፤ ተቃዋሚዎቻቸውን እንደ ንብ ወረው የሚያጠቁና የታዘዙትን ብቻ የሚፈጽሙ የፖለቲካ ስብስቦች (Sect or fundamentalist) ሆነዋል ቢባል ከውነት የራቀ አይሆንም። ብርሃኑ ነጋ እንደምናየው ከመሪነት አልፎ ዓምላካቸው ሆኗል። እሱን መተቸት ወንጀል የሆነበትና የሚያስቀጣበት ወቅት ላይ ደርሰናል። ይህ የፋንዳሜንታሊስቶች ዓይነተኛ ፀባይ ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ ጫካ ገባን ካላችሁ ፯ አመት አለፋችሁ፤ ገንዘብ መሰብሰብ ከጀመራችሁ ፲ ዓመት አለፋችሁ፤ ወያኔን ለማንበርከክ ፯ ወር ስጡን አላችሁ ሰጠናችሁ ሆኖም የጠረጴዛ ቴኒስ ስፋት ያለው ምድር እንኳን ነጻ አለወጣችሁም። ያማራው ገበሬ በሁለት ወር ውስጥ ወያኔን ሲያንቀጠቅጠው እናንተ የት ገባችሁ? ብሎ መጠየቅ የሚያስወነጅል ባልሆነ ነበር። ወያኔም ወገኖቻችን ግንባር ግንባራቸውን በጥይት የሚመታው ለምን ጠየቃችሁ ብሎ ነው።

አበበ በለው የመጀመሪያዎችን ጥያቄዎች በስነ ስርዓ ጠይቆ ከሄኖክ ትህትና የተሞላበት መልስ አግኝቷል። ነገሩ የተበላሸበት ከፌስቡክህ አገኘሁ ብሎ ሁለት የውሸትና አንድ ውነተኛ መረጃዎች ሲመዝ ነው። አንደኛው አፀያፊ ስድብ የተሞላበት ነው። ሁለተኛው ብርሃኑን በጅጉ የሚያሞግስ ሲሆን ምንጫቸው ደግሞ በሄኖክ ስም የተከፈተ የሃሰት አካውንት ነው። ሶስተኛው ከትክክለኛው የሄኖክ ፌስቦክ የመጣ ነው። ሄኖክ ቀደም ሲል ለአንባቢዎቹ በስሙ ብዙ አካውንቶች ተከፍተው ስድብና ብልግናን በማሰራጨት ላይ መሆናቸውን አስታውቋል። ይህን ጠንቅቆ የሚያውቀው አበበ እንደ ጋዜጠኛነቱ የመጀመሪያ ሥራው የምንጬን ትክክለኛነት ማጣራት ነበር። የፊስቡክ አካውንት እንደሚጠለፍና የሃሰትም አካውንት በመክፈት ብዙ ወንጀሎች እንደሚሰሩ እንኳን ለባለሙያው አበበ ለተራው ዜጋም የአደባባይ ሚስጥር ነው። የቴክኒክ ችሎታ ካነሰው አዋቂዎችን ማማከር፤ ቅንነት ካለው ደግሞ ሄኖክን ራሱን በቀጥታ መጠየቅ በቻለ ነበር። አበበ ግን የጋዜጠኛ ኤቲክስን በመጣስ በቀጥታ ይህ ከአንተ አካውንት የተገኘ ነው። ተቀበለው አነብልሃለሁ። መከላከያህ ምንድን ነው? በማለት ደረቅ ጥያቄውን ትንፋሽ እስከሚያጥረው ደጋገመው። ሄኖክም በትህትና ጽሁፉ የርሱ አለመሆኑን በተደጋጋሚ ቢገልጽም አበበ የሚቀበልና የሄኖክን መብት የሚያከብር አልሆነም። በዚህ ጊዜ ሄኖክ አበበ የሚያደርገው ብልግና መሆኑን ነግሮ ይቅርታ እንዲጠይቅ ቢያሳስበውም አበበ ወደ ሚቀጥለው ጥያቄ ከመሄድ ይልቅ ሄኖክ የራሱ ባልሆነ ጽሁፍ ላይ መልስ እንዲሰጥ ማስገደዱን ቀጠለ። በዚ ሁኔታ ውይይቱን መቀጠል ፋይዳ እንደለለው የተረዳው

ሄኖክ ስልኩን በመዝጋት ውይይቱን አቋረጠ። አበብ ይህ የሃሰት ማስረጃ ይዞ ዜጎችን መወንጀልና ዘብጥያ መወርወር የትግሬ ወያኔ ዋነኛ ስልት መሆኑን እንደሚያውቅ አልጠራጠርም። ጥያቂው አበበ ለምን ይህን ማድረግ ፈለግ ነው።

አበበ ቃለ መጠይቁ ባለመሳካቱና ግቡን ባለመምታቱ ብስጭቱን መግታት አለመቻሉን ሄኖክ ከሄደ በኋላ ባደረገው ሽንፈትን የመሸፈኛ  ቅጥ ያጣ ንግግሩ በግልጽ አሳይቷል።  ሄኖክ አበበን ባለጌ ብሎታል። ይህም ስህተት አልነበርም። ሄኖክ ጽሁፉ የኔ አይደለም ብሎ ደጋግሞ ቢነግረውም አበበ ግን ያንተ ነው እመን መከላከያህ ምንድን ነው ብሎ የሚያስገድድ ሰው ባለጌ ብቻ ሳይሆን ወንጀለኛም ነው። ለዚህ ጥፋቱን ተቀብሎ ይቅርታ መጠየቅ እንጅ ሰደበኝ ብሎ ማማረር ባልተገባው ነበር። የአማራው መደራጀት ደጋፊ በመምሰል ውንጀላውንና ወቀሳውን አምበልብሎታል። አማራውን እናደራጃለን የሚሉት ግለሰቦች ጊዚያቼውን የሚያጠፉት ሌላውን በመንቀፍ፤ በመተቸና በመሳደብ እንዲሁም የዓማራውን መደራጀት ከብዙ ነገር ጋር ስላላተሙትና ስላወሳሰቡት ለዓማራው መደራጀት እንቅፋት ሆነዋል የአዞ እንባውን አፍሷል። ከዚህም አልፎ የአማራውን ጥያቄ በግለሰብ በተለይም  በሄኖክ ዙሪያ እንዲሽከረከር ስለሚደረግ ጥያቂዎችን በጥሞና ከመመለስና ከማስረዳት ይልቅ ስድብ ይቀድማቸዋል ሲልም ይከሳል።

አበበ ፖለቲካን የማይለወጥና ከጊዚው ጋር የማይሄድ ባለቤት የለለው ቋሚ ግንብ አርጎ ያየዋል። በመሆኖም ሄኖክን ከብዙ አመታት በፊት የነበረውን አቋም ቀይሮ ግንቦት ሰባትን በመተቸቱ ስኆ የተናገርከውን ማክሰኆ ካልደገምከው እንዴት እንመንህ ሲል ያማራል። ፖለቲካ ተለዋዋጭ ነው። የትናንት ፖለቲካ ለነገ አይሰራም። አበበ ይህን ያህል ዓመት አሜሪካ ኖሮ ካልተረዳው በኔ ጽሁፍ ይረዳዋል ብየ አላምንም። ሆኖም የራሱ ድርጅት መሪ ብርሃኑ ነጋ ያደረገውን ግዙፍ የአቋም ለውጥ ላስታውሰው። በ1997 ከምርጫው በፊት ይሁን በኋላ አላስታውስም ስቶችክሆልም በተደረገ ሕዝባዊ ስብሰባ እንዲህ ብሏል፡፡ ***የትጥቅ ትግል ጊዜው ያለፈበት የትግል ስልት ነው። የትጥቅ ትግልን እንደ አማራጭ የሚቀበሉት ከጊዜው ጋር መራመድ የማይችሉ ብቻ ናቸው። ብቸኛ አማራጩ  ሰላማዊ ትግል ነው ካለ በኋላ ወያኔ አትበሉ ኢሕአዴግ በሉ ብሎን ነበር የሄደው።*** ይህ አባባሉ በትጥቅ ትግል ላይ ለተሰማሩትና በዝግጅት ላይ ለነበሩት ለዓመታት ትልቅ መሰናክል በመሆን ትግሉን አንቆ ይዞት ቆይቷል። እንደምናውቀው ከተወሰነ ዓመት በኋላ ብርሃኑ ትጥቅ ትግል ለዚያውም በኤርትራ በኩል እንጅ ሌላ ምርጫ የለም አለ። ታዲያስ? ብርኃኑ ድሮ ሰላማዊ ትግል ብቻ ብሏልና የትጥቅ ትግል አንቀበልም እንበል? ጥያቄው የትጥቅ ትግልን የመረጠው አምኖበት ነው? ከሆነስ ዓላማው ምንድን ነው፤መነሻና መድረሻውስ የት ነው? የሚለው እንጅ አቋሙን መቀየሩ አልነበረም። በዚህም አልተወቀሰም።

ለመሆኑ ዓማራው ለመደራጀት ጥረት ባደረገ ቁጥር አትደራጅም ብለው ያለ የሌለ ኃይላቸውን አሰባስበው በዓማራው ላይ የሚረባረቡት ነብሰበላዎች ኢትዮጵያን ባጠፏትና ሊያጠፏት በሚደራጁት ወንጀለኞች ላይ አፋቸው ከመለጎም አልፎ በጭብጨባ የሚያጅቧቸው ለምን ይሆን? ስየ አብርሃ፤ አስራት ገብሩ፤ ነጋሶ ጊዳዳ፤ አረጋዊ በርሄንና ሌሎችንም ባንዳዎች በጭብጨባ የሚቀበል ቡድን የኑሮን ጣም ያላዩትን ለጋና ወጣት የአማራ ታጋዮች በሳት መጥበስ ለምን አስፈለገ? አብርሃ ደስታን እንደጀግና የሚቀበል ስብስብ ሌላው ቢቀር የሄኖክን ስብእና ማክበርና መቀበል ካቃተው የፖለቲካ ሳይሆን የአእምሮ ቀውስ ችግር እንዳለበት አመላካች ነው። በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ያማራ ጭንቅላት ቆርጠው የሚሰቅሉ፤ ከነነብሱ ገደል የወረወሩን፤ ማህፀን ቀደው ፅንስ የሚያወጡ፤ ሚስትን በባል፤ ልጅን ባባት የሚያስገድሉ፤ ጡትና ብልት የሚቆርጡ አውሬውች፤ የልብወለድ ታሪክ ደርሰው፡ ምስኪኑን ዓማራ በቅኝ ገዥነት ወንጅለው ዓማራውንና ኢትዮጵያን  ለማጥፋት የራሳቸውን ባንዲራ ይዘው የሚሮጡትን ተገንጣዮች በክብር የሚያስተናግዱ፤ ዓማራን ለማጥፋት ጦር አሰልጥነው በአዝማችነት የመሩትን ሌንጮንና ዲማነጎን በክብርና በጭብጨባ የሚያስተናግድ ግንቦትት ፯ ን ለመተቸት ያልደፈረ ተከታይና ጋዜጠኛ በአማራው ላይ ብቻ ሳይሆን በራሱ ላይም ሞት የፈረደ መሆኑን እንዴት ሳተው?

ግንቦት ሰባት ኢትዮጵያውያንን ያሰባሰበ ድረጅት ሳይሆን ዓማራውን ለማስመታት ኢትዮጵያዊነትን እንደሽፋን የሚጠቀም የደቡብና የኦሮሞ ብሄርተኞች ድርጅት ነው። ለዚህም ዓላማው ሌንጮንና በአማራ ጥላቻ የተለከፉትን ወንጀለኞችና አንዳንድ የአማራ ተናጋሪዎችን አካትቷል። አይደለም ከተባለ በአመራር ላይ ያሉ ዓማሮችን ጥቀስልኝ። ከአማራው የሚፈለገው የገንዘብ ድጋፉ እንጅ የፖለቲካ ተሳትፎና መሪነቱ አይደለም። የማይነጥፍ የኤኮኖሚ ምንጭ ነውና።

በመጨረሻም አማራው ከንግዲህ እራሱን ለመከላከል ቆርጦ ተነስቷል። ስም ቢጠፋ ሰማይ ቢቧጠጥ ከንግዲህ የሚያግደው ምድራዊ ኃይል የለም። በክቡር አሥራት ወልደየስ፤ በኃይሉ ሻወል፤ ታየ ወልደሰማያትና በሌሎችም ላይ የተደረገው ሴራ መልኩን ቀያይሮ ቢመጣ አይሰናከልም። አማራው የሰንካላና የተንኮለኛ ድርጅቶች ሰለባ ላይሆን ቆርጧል፡፤ የቁርጠኝነቱ መነሻም የተፈጸመበት ግፍ እንጅ የዲሞክራሲ ወይም የስልጣን ሱሰኝነት አይደለም። አማራው ኢትዮጵያዊነቱን በምንም ተአምር አይተውም። ሆኖም ቅድሚያው ራሱን ማዳን እንጅ ኢትዮጵያን መገንባት አይደለም። ይህ የሁሉም ግዴታ ነው። የአማራው ብቻ አይደለም። አማራውን ከሚያከብሩ ማናቸውም ድርጅት ጋር አብሮ ይሰራል። ራሱን ግን በማንም ላይ ጥገኛ አያደርግም። አማራው ራሱን ሲያድን ኢትዮጵያን ይገነባል።

አበበ በለው ዘሩ ምን እንደሆነ አላውቅም። የዓማራ ስም ይዘው አማራውን የሚያደናግሩ እንዳሉ ግን እናውቃለን። እነሱም ቀስ በቀስ ይለያሉ።

*ታምሩ ሁነኛው*